# የጎሰኞች የሃያ ዓመት ቲያትር በሆሆታ ተከፈተ

**ጌታቸው ኃይሌ**

አሜሪካ የሚኖር ሁሉ እንደሚያስታውሰው ፥ አዲስ የቲያትር ፊልም ሲወጣ ለመጀመሪያ ጊዜ በየሲኒማ ቤቱ በታላቅ ሆሆታ ይታያል ። ቲያትሩ ቀደም ብሎ ብዙ ስለተወራለት ሰዉ የመግቢያ ዋጋ ከፍሎ ለማየት በየሲኒማው በር ተሽቀዳድሞ ይሰለፋል ። የፊልሙ (የቲያትሩ) ተፈላጊነት የሚገመተው በዚያ በመጀመሪያው ዕለት በተሸጠው ቲኬትና በተገኘው ገቢ ብዛት ነው ። እውነተኛው ትችትና ግምገማ የሚጀምረው ግን ሕዝቡ ይህን ብዙ የተወራለትን አዲስ ፊልም አይቶና ታዝቦ ሲወጣ ነው ።

ቲያትሩን ተወዳጅ የሚያደርጉት ሁለት ነገሮች ናቸው ፤ አንደኛው መሐደምቱ (ልብ ወለዱ ታሪክ) ነው ። መሐደምቱ ፈጠራ ቢሆንም ፥ ለቲያትርና ለፊልም ደረጃ የሚያበቃው መጀመሪያ በመጽሐፍ መልክ ወጥቶ ከአንባቢዎችና ከገምጋሚዎች ዘንድ አድንቆት ሲያተርፍ ነው ። አጻጻፉ ወደ እውነተኝነት ፍጹም በሆነ ደረጃ መጠጋትና የታሪኩም ፍጻሜ በደስታ የሚያሰክር መሆን አለበት ። የመሐደምቱ ታሪክ መጽሐፍ ሆኖ ሲነበብ አድናቆት ካላተረፈ መጀመሪያውኑ ለቲያትርና ለፊልም አይታጭም ። አድናቆት የሚያተርፈው ውሸቱ የፈጠራ ታሪክ እውነት መስሎ ሲፈጠር ነው ። መሐደምት የሚደነቀው ጥሩ ጸሐፊ ፥ ማለት ጥሩ ዋሺ ፥ ዋሽቶ ሲጽፈው ነው ።

ሁለተኛው የተዋናዮቹ ተውኔት ነው ። መደነቅን እንዲያተርፉ የውሸቱን (ማለት የፈጠራውን) ታሪክ በመድረክ ላይ ወጥተው በተግባር ሲያስተጋቡት ፍጹም እውነት እያስመሰሉ መሆን አለበት ። ፈገግታ በሚያስፈልግበት ፈገግ ሲሉ ፥ ማልቀስ በሚያስፈልግበት ዕንባ እያወረዱ ሲያለቅሱ ፥ ጭካኔ በሚያስፈልግበት ተመልካችን በሚያናድድ ደረጃ ሲጨክኑ ፥ በቀል በሚያስፈልግበት ተመልካችን አንጀት በሚያርስ ደረጃ ሲበቀሉ ታሪኩን ከመሐደምትነት አውጥተው እውነት እንዲመስል አድርገው በተግባት ማሳየት አለባቸው ። ውሸቱን እውነት ማስመሰሉን ካሳመሩት በዓመቱ መጨረሻ ሽልማት ያገኙበታል ።

ወደ መሐደምቱ ታሪክ ልመለስ ። አንድ ጊዜ አንዱን ፈላስፋ ፥ "ምንትኑ ፡ ውእቱ ፡ ግብር ፡ ዘይበቍዕ ፡ ወኢያቴክዝ ፡?" (ጸጸት የሌለበት ጠቃሚ ነገር ምንድነው?) ቢሉት "ሞተ ፡ ሰብእ ፡ እኩያን ፡" (የክፉ ሰዎች ሞት ነው) አለ ይባላል ። ታላላቅ መሐድምት የተመሠረቱት እዚህ እምነት ላይ ነው ። ጸሐፊው ፈጠራውን አንድ ቢሞት የማያሳዝን ክፉ ሰው በመፍጠር ይጀምራል ። ለምሳሌ ፥ አንድ መልከ ጥፉ ሰው ሰዎች በሰላም ከተኙበት ሌሊት በራቸውን ሰብሮ ገብቶ ሰዎቹን አስሮ ሕፃናን

ልጅ ከወላጆቿ ፊት ፥ ወይንም ሚስትዮዋን በባሏ ፊት ደፍሮ ገንዘብ ዘርፎ ይሄዳል ። ይኼ ሰው አያናድድም? ተይዞ በጥይት ቢደበደብ ማን ያዝንለታል? ጭካኔው የተገለጸው በመጽሐፍ ከሆነ አንባቢውን ፥ በፊልም ከታየ ተመልካቹን ያሳዝናል ፤ ይናድዳል ። ወንጀሉ ለፖሊስ ተነግሮ ኀሠሣው እንዲጀመር ይጓጓል ። ፖሊሶቹ ሰምተው ቺላ ሲሉት ፤ ወይም ክስ አቅራቢዎቹ ያቀረቡት ክስ ፈጠራ እንጂ በውን እንዲህ ያለ ወንጀል እንዳልተፈጸመ አድርገው ሲያዩት አንባቢው/ተመልካቹ የባሰውን ይበሳጫል ። ፊልሙ የሰውን ስሜት እንደዚህ ከቀሰቀሰ ጸሐፊው ጥሩ ፈጣሪ ነው ።

በሲኒማው ቤት ውስጥ ያሉት ተመልካቾች "ወንጀለኛው" በር ሰብሮ ገብቶ ያደረገውን አድርጎ ሲሄድ በፊልሙ ውስጥ በዓይናቸው ስላዩ ፥ ወንጀለኛው ሳይያዝና ፍርዱን ሳያገኝ ታሪኩ በምንም ምክንያት ማለቅ የለበትም ። ደራሲዎች ሰውን የሚያስደስተው ፍቅር ወይም "ሞተ ፡ ሰብአ ፡ እኩያን ፡" (የክፉ ሰዎች ሞት) እንደሆነ ያውቃሉ ። የጥቅም ጉዳይ ስለሆነ ፥ የሚፈልጉት ሰውን ለማስደሰትና ፊልሙን ተመልሰው መጥተው እንዲያዩ ለማድረግ ፥ ያዩም ለሌሎች እንዲያሰሙ እንጂ ፥ አሳዝኖ ለመሸኘት አይደለም ። "ፖሊስና እርምጃው" የሚባለውን ጋዜጣ እናነብ የነበረው ወንጀል የተፈጸመባቸው ሰላማዊ ሰዎች እነማን እንደነበሩ ለማወቅ ሳይሆን ወንጀለኛው ተይዞ ፍርዱን ሲያገኝ አይተን ለመደሰት ነበር ።

የመሐደምት ደራሲዎች ከሚያደርጉት ጥንቃቄ ሁሉ ዋናው ነጥብ ወንጀለኛ ያደረጉት ሰው በምንም ዓይነት ፥ በመልኩም እንኳ ቢሆን ፥ አሳዛኝ እንዳይሆን ነው ። ፖሊስ ሲደርስበት ተመልካቹ ቅቤ እንዲጠጣ ፤ ሲሰቀል አንጀቱ እንዲርስ ማድረግ አለባቸው ። በእውነት ሕይወት እንኳ ሙሶሊኒ ሲሰቀል የዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን እንደተደሰቱ መገመት ይቻላል ። በሰላም አርጅቶ ቢሞት ኖሮ የስንት ሰው ቆሽቴ ያርር ነበር!! ሩቅ ሳንሄድ ቢን ለዲን በጥይት ተደብድቦ መሞቱ ሲሰማ ጭፍሮቹ ማዘናቸው ቢታወቅም ፥ ኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ መንታ ጥቅሞች (Twin Towers) ከፈረሱበት አጠገብ የተሰበሰበው ሕዝብ ደስታ የቱን ያህል እንደነበረ ብዙዎቻችን አይተናል ።

አንድ ጸሐፊ ያንን ያህል ደስታ በሰው መንፈስ መቀስቀስ ዋና ምኞቱ ስለሆነ ፥ የቢን ለዲንን ያህል የሚጠላ ክፉ ሰው ፥ እንዲያውም ጠላት ፥ መፍጠርና በመጨረሻም ሲሞት ማሳየት አለበት ። ፊልሙም በፍጹማን ዋሺዎች ተሠርቶ በብዙ ሆሆታ ይከፈታል ብያለሁ ። እንግዲህ ቅዳሜ ግንቦት 20 ቀን (May 28) በታላቅ ሆሆታ የተከፈተው የጎሰኞች ሃያኛው ዓመት የመሐድም ቲያትር ይኼ ነው ። ሲገደል የሚያስደስት ጠላት የተፈጠረበት የፈጠራ ታሪክ በቡድንና በተናጠል ሲጻፍ ብዙ ጊዜ ፈጅቷል ።

በጎሰኞቹ ጭንቅላት ወንጀለኛው ጠላት አማራው ፥ ሰለባው ደግሞ የትግራይ ሕዝብ መሆናቸው ገና ከጥንቱ ከጠዋቱ ቢነደፍም ፥ የአጻጻፉ ዘዴ የተተለመው በጸሐፊዎቹ ሳይሆን በቅጥረኞች የሥነ ልቡና

ሊ.ቃውንት ነው ። የሚያናድድ ጠላት የመፍጠር ዕውቀት ያላቸው እነሱ ናቸው ። በፈጠራው ውስጥ ሁለት ነጥቦች መካተት አለባቸው ፤ <u>አንደኛ</u> ፥ ወንጀሉን ከባድ ለማድረግና ሰለባዎች ናችሁ በተባሉት ዘንድ ታማኝነት እንዲያገኝ አማራው በምን በምን ይወንጀል? ሰለባዎቹ ወንጀሉ እንዲሰማቸው አማራው ምን ምን አደረጋችሁ ተብሎ ይነገሩ? <u>ሁለተኛ</u> ፥ ትግሬዎቹን ብቻ ሰለባ ማድረግ አያዋጣም ። ብዙ ደጋፊ ለመለምለም አማራ ያልሆነውን ሁሉ የአማራው ሰለባ ማድረግ ያስፈልጋል ።

እንግዲህ አማራው አማራ ያልሆነውን ሁሉ ፥ ሕፃን ልጅ ፥ ሴት ፥ ሽማግሌ ፥ በሽተኛ ሳይል በጥይት የሚደበድብ ፥ የእርጉዝ ሆድ በሾተል የሚዘከዝክ ፥ ደሙ መጠጣት ያለበት ጨካኝ ጠላት ይደረጋል ። አማራው ትግሬውን ፥ ኤርትራዊውን ፥ ኦሮሞውን ፥ ሐዲያውን ፥ ዉጋዴኒውን ፥ አደሬውን ፥ ወላይታውን ፥ ወዘተ የፈጀው ፥ በሰላም ከሚኖሩበት ድረስ መጥቶ የቅኝ ግዛት አድርጓቸው ነው ። የፈጠራው ታሪክ ይኼ ነው ። ቲያትሩን ሽልማት በሚያሰጥ ደረጃ እየዋሹ የተጫወቱት መለስ ዜናዊና ካድሬዎቹ ናቸው ።

ታሪኩ ረጅም ነው ፡ አማራ ያልሆነውን ሁሉ ያስራብ አማራ ነው! ትግራይን በድርቅ እንድ ታልቅ ያደረገው አማራ ነው! የትግሬዎችን ጀግንነት ለራሱ አድርጎ ታሪክ የጻፈው አማራ ነው! የኦሮሞን ሕዝብ በቅኝ ግዛት ረግጦ የገዛው አማራው ነው! ከራሱ ቋንቋ ከአማርኛ በቅር ማንም ሰው በሌላ ቋንቋ እንዳይናገር የከለከለው አማራው ነው ። በፊት የንጉሡ አጃቢ በኋላ ደግሞ የደርግ አባል ሆኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሠቃየ አማራው ነው ። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎችን ማለቂያ የሌላቸውን የአማራ ወንጀሎች የሚያብራሩ መጻሕፍት በትግርኛ ፥ በአማርኛ ፥ በእንግሊዝኛ ጻፉ ። የኢትዮጵያን እውነተኛ ታሪክ የመዘገቡትን መጻሕፍት ብዙዎቹን እያደኑ ከየቤተ መጻሕፍቱ አወደሟቸው ።

ሊጠፉ ያልቻሉ ሰነዶች ሌላ ትርጉም ሰጧቸው ። ሕዝቡንም ታሪክ የሌለው ሕዝብ እያደረጉት ነው ። ለምሳሌ ፥ ደቂቀ እስጢፋኖስ የዛሬ አምስት መቶ ሰባ አምስት ዓመት ባነሡት የሃይማኖት ጭቅጭቅ ምክንያት የደረሰባቸውን ሥቃይ የአማራው መንግሥት በትግሬዎች ላይ የፈጸመው ወንጀል አድርገው አቅርበውታል ። እውነቱ ግን እንዲህ አልነበረም ። የደቂቀ እስጢፋኖስ ንቅናቄ የተጀመረው ትግራይ ውስጥ ቢሆንም ፥ ተከታዮቹና ሥቃዩን የቀመሱት ትግሬዎች ብቻ አልነበሩም ፤ የራሱ የንጉሡ ልጆች ሳይቀሩ ነበሩበት ።

ፈጠራው ብዙ የተቆጡ አንጎላቸው በፕሮፓጋንዳው የተበላሸ ተከታዮች አፈራ ። ቁጡ አውሬዎች ለማፍራት የኢትዮጵያ መሬት የተመቸ ነበር ። በየወረዳው ደኻና በሽተኛ ፥ በጠቅላላው ሕይወት ያስጨነቀችው ስለሞላ ፥ አማራ ካልሆነው ውስጥ ብዙዎች እንደዚህ ቀን የጐደለባቸው እውነትም በአማራው ወንጀል መሰላቸው ። የተነገራቸውን አመኑ ። አማሮች ወደሚኖሩበት አገር ሄዶ አማራው

እንዴት ተኮራምቶ እንደሚኖር አላዩም ። አለማየታቸው ፥ አለማወቃቸው መሐደምት ጸሐፊዎች ወንጀሉን የፈለጉትን ያህል ለመቆለል አመቻቸው ። የንጉሡ አጃቢዎች ሁሉም አማርኛ ስለሚናገሩ ፥ ኤርትራውያን ፥ ትግሬዎች ፥ ኦሮሞዎች ፥ አማሮች ፥ ጉራጌዎችና ሌሎችም ሁሉ ወይም ድብልቆች መሆናቸውን አላወቁም ፤ ሁሉም አማሮች መሆናቸውን ፥ አማሮች ካልሆኑም የአማራው አገልጋዮች መሆናቸውን እንደተነገራቸው አመኑ ።

በሌላ ጊዜ እንደጻፍኩት ፥ ከእነዚህ አማርኛ ተናገሪ ትግሬዎችና ኤርትራውያን ውስጥ ብዞዎቹ በአማራው ስም ብዙ ወንጀል ፈጽመዋል ። አማርኛ በመናገር አማራ እየመሰሉ ኦሮሞዎቹን አዋርደዋል ፤ "አህያ ፥ ተብታባ" ፥ እያሉ ሲሳደቡ ተሰምተዋል ። ዓላማቸው ፈጠራ ጸሐፊዎቹ "የአማራ ወንጀል" እያሉ የሚጽፉት ወንጀል እውነት እንዲመስል ነው ። የኦሮሞ ገበሬ በአማርኛ እንዲህ ሲሰደብ ፥ አማራ ሰደበኝ ይላል እንጂ ሽረኛ ትግሬ ወይም ተንኮለኛ ኤርትራዊ ሰደበኝ ለማለት ምን ችሎታ አለው? እንኳን ገበሬው እኛም ብንሆን ኢትዮጵያን በይፋ እስከከዱ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እንጂ ትግሬዎችና ኤርትራውያን መሆናቸውን አናውቅም ፥ ብናውቅም አይገደንም ነበር ።

ይኼ እንግዲህ የትግራይን ሕዝብና ሊላውን አማራ ያልሆነውን በአማራው ላይ ለማስነሣት የተደረገ ቅስቀሳ ነው ። በኦርቶዶክሶቹም ላይ ሙስሊሞቹንና ኦርቶዶክስ ያልሆኑትን ክርስቲያኖች ማስነሣት ዋና እርምጃ ነው ። ጎሰኞቹን መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባይቀድማቸውና ሁኔታውን ባይለውጠው ኖሮ ፥ የአማራው መንግሥት እስላሞችን ይበድላል ብለው እስላሞቹን ያስነሡ ነበር ። ሆኖም ተቀደምን ብለው አልተዉትም ፤ ኦርቶዶክሶቹ ጥቂቶች በሆኑበት አገር እስላሞቹ እንዲያጠቋቸው ሁኔታውን አመቻችተውላቸዋል ። ኦርቶዶክስ ያልሆኑት ክርስቲያኖችም ገርዎቹ ወገኖቻቸው ከኒሻዎች ስለሆኑ ፥ መሃይምናኑና ደብተራ-መሰሎቹ የሚለፈልፉትን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እያስመሰሉ ጥንታዊቷንና ባለታሪኳን ቤተ ክርስቲያን ለማጥቃት ይሞክራሉ ። ቤተ ክርስቲያኗ መከታ ያጣችው ፥ ዶክተር ጳውሎስ የትግራይ ልጅ በመሆናቸው ፓትሪያርክነት የሆኑ ዕለት ነው ።

አማራው እውነት እንዲህ በሌሎቹ ላይ ይኸን ያህል በደል ያደረሰ ከሆነ ፥ ድምጥማጡ ቢጠፋ ሌሎቹ ደስታቸው ከፍ ያለ ቢሆን አያስገርምም ። የፊልም መጨረሻው ይኼ መሆን አለበት ። ቅዳሜ ግንቦት 20 ቀን (May 28) በታላቅ ሆሆታ የተከፈተው የጎሰኞቹ ሃያኛው ዓመት የመሐድም ቲያትር ይኼ ነው ። አማራውና ተንከባክቦ ያቆየልን ኢትዮጵያ ሃያ ዓመት ሙሉ የተቀጠቀጡበት በዓል ተከበረ ።

ግን አማራው እውነት ይኸን ያህል አውሬ ነው? እውነት እንዲህ በሌሎቹ ላይ ይኸን ያህል በደል ለማድረስ መብት ነበረው? እውነትና እምነት የተለያዩ ናቸው ። ማንኛውም ታሪክ ከታመነበት ለሚያምነው ሰው እውነት ይሆናል ። ከእምነት ወጥተን ማሰብ ከጀመርን ግን በማንኛውም ኅብረተ

ሰብ ውስጥ--ኦሮሞ ፥ ትግሬ ፥ አማራ ፥ ጀርመን ፥ አሜሪካ . . . ሳይል ፥ በሁሉም ዘንድ ደግ ፥ ክፉ ፣ ጀግና ፥ ፈሪ . . . ይኖራል ። ጠቅላላው ኅብረተ ሰብ ግን "ደግ ፥ ክፉ ፣ ጀግና ፥ ፈሪ . . ." አይሆንም ። ይሆናል የሚል ካለ ፥ ዕውቀት የጐደለው ደንቆሮ ሰው ነው ። የሠለጠነው ዓለም በእንዲህ ያለ ድንቁርና ለብዙ ዘመናት ተሠቃይቶ ፥ አሁን እንዲህ ያለው እምነት ከሕዝቡ አእምሮ እንዲፋቅ በልዩ ልዩ መንገድ እየጣረ ነው ። "ጥቁሮች እንዲህ ናቸው ፤ እንዲህ አይደሉም" እየተባሉ በዘር ልዩነት የተሠቃዩበት ዘመን በማለፍ ላይ ነው ። በእኛ አገር እስከዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ የኋላ ቀርነት አስተሳሰብ ጐልቶ አይታይም ነበር ። ቢኖር ኖሮ የአንዱ ብሔረሰብ ሰው ከሌላው ብሔረሰብ ሰው ጋር አይጋባም ነበር ። ጎሰኞቹ አማራን "ክፉ ፥ ጨካኝ ፥ አረመኔ ፥ ሰው-በላ" አድርገው የሣሉት አምነውበት ሳይሆን ፥ ያላንዳች ርኅራኄ የሚበቀል ተከታይ ለማትረፍ ነው ። ቀንቷቸዋል ።

ግን ለምንድን ነው በተለየ አማራውን ጠላት ያደረጉት? ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ ፤ ዋናው ግን ሰፊዋን ኢትዮጵያ ያወረሰን ጀግናው አማራ ስለሆነ ቀንተውበት ነው ። አማራው ይኸንን ታላቅ ታሪክ እንደሠራ ማንም አይክደውም ። ጎሰኞቹም "የአፄ ምኒልክ ነፍጠኛ በሕዝቡ ላይ ይኸን ወንጀል ፈጸመ" ሲሉ የጠፋውን መሬት አማራው መልሶ አቅንቶ ሰፊ አገር መፍጠሩን መናገራቸው ነው ። ግን አስቀኚው ታሪኩ አልዋጥ ስላላቸው ስለውጤቱ (ማለት ፥ በአማራው ጥረትና ጀግንነት አገሪቱ ስለመስፋቷ) ሳይሆን ስለ መንገዱ (ስለዘመቻውና ስለተፈጸመው ጭካኔ) መተቸት ይመርጣሉ ። ትችቱ የመንፈስ እርካታ ይሰጣቸዋል ። ትልቅን የሚያዋርድ ትልቅነት እንደሚሰማው የታወቀ ነው ።

ግን አማራ የሚሉት ማንን ነው? አማራ የሚሉት/ አማራ የሚባለው በትረ ሥልጣኑን ከዛጌ ቤተሰብ ወስዶ ፥ አገሪቱን እስከ ዘመነ ጎሰኝነት ድረስ ያቆያትን ሁሉ ነው ። ልብ እንበል ፤ በትረ ሥልጣኑን ከዛጌ ቤተሰብ የወሰደው አንድ የአክሱሙ ንጉሥ ዘር ነኝ ያለ ሰው ነው ። የአክሱም መንግሥት ሲፈርስ ንጉሡ ሸሽቶ አማሮች አገር ጥገኛ ሆኖ ነበር ። ልጆቹ ከአገሬው ጋር ተጋብተው ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው በባህል አማራ ይሆናሉ ። ከነሱ ውስጥ አንዱን እናት አባቱ ፥ "አምላክ ይሁነው" (ይኩኖ አምላክ) ብለው በግዕዝ ቋንቋ የመረቁት ምርቃት ይዞለት ፥ የአባቶቹን የአክሱም ነገሥታትን መንግሥት አስመለሰ ። መንግሥት ለመገልበጥ በዛጌዎች ላይ ሲዘምት የመለመላቸው ወታደሮች አማሮች አልነበሩም ፤ እንደ ዛጌዎች አገዎች ነበሩ ። አገዎች እንደ ኦሮሞዎችና እንደ ሱማሌዎች ብዙ ጎሳዎች እንጂ አንድ ሕዝብ አይደሉም ። ምናልባትም አንዱ ጎሳ ከሌላው ጎሳ ጋር በሰላም ጉርብትና አይኖርም ነበር ።

ይኩኖ አምላክና ዘሮቹ መንግሥታቸውን የዘረጉት አማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ መካከል ስለሆነ ፥ የቤተ መንግሥቱ መነጋገሪያ ቋንቋ አማርኛ መሆን አለበት ። መጻፊያው ቋንቋ ግን ያው የአክሱም ዘመነ መንግሥት ይሠራበት የነበረው ግዕዝ ነበረ ። ከንጉሡ ጋር ሆነው ይገዙ የነበሩት ገዢዎቹስ? ግዛቱ አምላካዊ (Theocracy) ስለነበረ ፥ ሥልጣኑን ከንጉሡ ጋር የያዙት አቡኑ ፥ እጨጌው ፥ ጵራድ

ማሰሬው (ንጉሥ የሚቀባው) ፥ ቄሰ ሐፄው (ማዕድ ባራኪው) ፥ ጸሐፌ ትእዛዞቹ ፥ ዐቃቤ ሕጉ ፥ ዐቃቤ ፍትሐ ፥ ዐቃቤ ሰዓቱ ፥ ጎዱግ ቃቄታቹ ፥ ሊቀ ማእምራኑ ፥ ብላቴን ጌታው ፥ ግራ ቀኝ ዳኞቹ ፥ ግራ ቀኝ ብሕት ወደዶቹ እና የየገዳሙ አበ ምኔቶች ነበሩ ። እነዚህ የሚመረጡት በዕውቀታቸውና በአገልግሎታቸው እንጂ ፥ በትውልድ ሀገራቸው በአድልዎ አልነበረም ። አገረ ገዢዎቹ ወይ የንጉሡ ወንድሞች ወይ የየሀገሩ ባላባቶች ነበሩ ። የንጉሡ የጦር ሠራዊት አማሮች ፥ ትግሬዎች ፥ ጉራጌዎች ፥ ወደኋላ ጊዜ ደሞ ኦሮሞዎች እና ሌሎችም ነበሩ ። እነዚህ ሹማምንት በዚህ መንገድ የመንግሥት ሥልጣን ተካፋይ ሲሆኑ ሁሉም አማራ ይባላሉ ። በገዢው አካባቢ ያለው ሕዝብ በደም ድብልቅ ፥ በባህል አማራ ነው ። ይህ በደም ድብልቅ ፥ በባህል አማራ የሆነው ሕዝብ ኢትዮጵያን ያቆየልን ደሙን አፍስሶ ስለ ሆነ ፥ ዛሬ ልጆቹ ለሀገሪቱ አንድነት ቢንገበገቡና ቢቆረቆሩ ፥ ብዙ አይገርመንም ።

የነገሥታቱ ፍርድ ቤትም ቢሆን ዳኝነቱ ዛሬ የምንነቅፈውን ያህል ፍርደ ገምድል አልነበረም ። የሚዳኙበት ፍትሐ ነገሥት የሚባል የሕግ መጽሐፍ ነበራቸው ። በጎንደር ዘመነ መንግሥት ዳኞች ለዳኝነት ግራና ቀኝ እንደተሠየሙ ፥ ከቅዱስ ያሬድ ድጓ ውስጥ "አመ ፡ ዕለተ ፡ ፍዳ ፡ ወአመ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፥ አመ ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፥ ምንተ ፡ ንብላ ፡ ለነፍስ ፡ (ሁሉም የጁን በሚያገኝባት በዚያች ዕለት ፥ በዚያች የፍርድ ዕለት ፥ በዚያች የእግዚአብሔር ዕለት ፥ ነፍሳችንን ምን ብለን ከኩነኔ እናድናታለን?) የሚለውን መዝሙር ሦስት ጊዜ እስከ ፍጻሜው ይዘምሩና የግዕዙን ትርጉምና የመዝሙሩን መንፈሳዊ መልእክት ከጽራግ ማሠሬውና ከሊቀ ማእምራን ይሰማሉ ። ሞተው ነፍሳቸው ከታላቁ ዳኛ ፊት ስትቀርብ ፍርድ አጓድላችኋል እንዳይባሉና እንዳይፈረድባቸው ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸው ነበር ማለት ነው ። ፈሪሀ እግዚአብሔር ስለነበረባቸው ፥ በስጋት ያዳምጣሉ ። መሬት ሲንቀጠቀጥ ፥ ጨረቃ ደም ስትለብስ ፥ አምላክ መቆጣቱ እንደሆነ ይገባቸውና ይገሠጹ ነበር ። እነዚህ ያለፈውን የሚኮንኑ ጎሰኞች አሁን ሥልጣኑን ሲይዙ መበልጸጊያና የፈጠራ በቀል መፈጸሚያ ከማድረግ በቀር ሌላ ምን አደረጉበት?

ድርሰቴን ከሲራክ ጥበብ በአንዲቷ ትዝብት ልደምድመው ፤

> ወለእመ ፡ በኵሉ ፡ ወደቀ ፥ ኢትደቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸላኢከ ። ወለእመ ፡ ኵሉ ፡ ተበቀለከ ፥ ጸላኢከ ፡ ኢይትበቀልከ ። አልቦ ፡ ርእስ ፡ ዘየአኪ ፡ እምርእሰ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፤ ወአልቦ ፡ ቂም ፡ ዘየአኪ ፡ እምቂመ ፡ ጸላኢ ።
>
> የትም ብትወድቅ ፥ ጠላቱ ባደረህ እጅ አትውደቅ ። ማንም ቢበቀልህ ፥ ጠላቱ ያደረህ አይበቀልህ ። ከእባብ ራስ የሚከፋ ራስ የለም ፤ ጠላቱ ካደረህ ሰው ቂም የከፋ ቂም የለም ።